አዋጅ ቁጥር 14/1994

የ1994 ዓመተ ምህረት የተሻሻለው የአፋር ክልል ህገ መንግስት ማፅደቂያ አዋጅ

በክልሉ ነዋሪ ሕዝብ ተወካዮች ተመክሮበት የካቲት 19/90 ዓ.ም በመጀመሪያ የፀደቀውን እና እስከአሁን ሲሰራበት የቆየውን የክልሉን ህገ መንግስት በጥልቀት ተመልክቶ በተለይም የክልሉን የመንግስት አካላት የስልጣን ክፍፍልና ተጠያቂነት በግልፅ መደንገግና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት መስጠት በሚቻልበት ሁኔታ ህገ መንግስቱን ማሻሻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ በአዋጅ ቁጥር 1/1990 ዓ.ም በፀደቀው የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀፅ 99 መሠረት ከዚህ የሚከተለው የተሻሻለው የ1994 ዓመተ ምህረት የአፋር ክልል ህገ መንግስት ማፅደቂያ አዋጅ ታውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የተሻሻለው የ1994 ዓመተ ምህረት የአፋር ክልል ህገ መንግስት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር 14/1994 ዓ.ም ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

1. የተሻሻለው የ1994 ህገ መንግስት ስለመፅደቁ

በአዋጅ ቁጥር 1/1990 ዓመተ ምህረት የፀደቀው የክልሉ ህገ መንግስት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ ከታየ በኋላ የተሻሻለው የ1994 ዓመተ ምህረት የአፋር ክልል ህገ መንግስት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

2. ስለነባር ሕጐች ተፈፃሚነት

በሥራ ላይ ያለ ማንኛውም ነባር ሕግ ከተሻሻለው ሕገ መንግስት ጋር ከታቃረነ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከቀን 28/10/1994 ዓመተ ምህረት ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ሰኔ ***28*** ቀን ***1994*** ዓመተ ምህረት

እስማኤል ዓሊ ሲሮ

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

መግቢያ፣

እኛ የአፋር ሕዝብ ለዘመናት ተንሰራፍቶ በቆየው አፋኝ ስርዓት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችን ታፍነው በተዛቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ለድህነትና ኋላቀርነት አጋልጠውን በመቆየታቸው በአጠቃላይ እድገታችን ላይ የደረሱትን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለማስወገድ በመፈለግ፣

የአፋር ሕዝብ ያለፉት የኢትዮጵያ ጨቋኝ ሥርዓቶችን ለመደምሰስ ወደር የሌለው መስዋእትነት ከከፈለባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ሁሉም ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው የተከበሩ ሕዝቦች በህገ መንግስትና በሱ ብቻ የምትመራ ዴሞክራሲያዊት ሀገር እንድትሆን በማለት በአብዛኛው የሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ላይ ይፈፀም በነበረው አንገፍጋፊ ጭቆና ተጎጂ ሆነን መቆየታችን በማያዳግም ሁኔታ መታረም እንዳለበት በማመን፣

መላ የሀገራችን ብሄር፣ ብሄረሰቦች፣ ሕዝቦች ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ አድሃሪውና አፋኙ ስርዓት በሚያስተማምን ሁኔታ ተደምስሶ ኢትዮጵያ ሀገራችን የግለሰብ መብቶችና የብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል የተከበሩባት አጠቃላይ የህግ የላይነት የነገሰባት ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መሆንዋ የጋራ እድገትን ለማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ለማነፅ ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ፣

እኛ የአፋር ሕዝብ ለፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ለዘላቂ ሰላም፣ ጠንካራ ዲሞክራሲ የምንበቃ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት መሰረት ያደረገና ከብሔራዊ ክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ህግ የተዛመደና የዚህ ክልል ሕዝቦች የተከበሩበትና ሕገ መንግስታዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችለን የራሳችን ህገ መንግስት ሲኖረን መሆኑን በሚገባ በማመን፣

በሥራ ላይ ያለው ህገ መንግስት ከክልሉ ነባራዊ የእድገት ደረጃና የህብረተሰብ አኗኗር ጋር የተዛመደና ግልፅ አሰራርን የሚከተል በመረጠው ሕዝብ ተጠያቂ የሚሆንና ብቃት ያለው መንግስታዊ አደረጃጀትን በሚያሳይ አግባብ ጥልቅ መስተካከል ተደርጎበትና የምንገኝበት ሁኔታ በሚጠይቀው መጠን እንደገና ተሻሽሎ መውጣት ያለበት መሆኑን በውል በመረዳት እነሆ ዛሬ 28/10/94 ዓ.ም በሠመራ ከተማ ባካሄድነው የክልል ምክር ቤት ጉባኤ ለዚሁ ዓላማ በተሰየመ አካል ተረቅቆ በቀረበው የተሻሻለው ህገ መንግስት ላይ መክረንና በዝርዝር ተወያይተን ሰነዱን በሙሉ ድምፅ አፅድቀነዋል።

ምዕራፍ አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀፅ 1

የክልሉ መንግስት ሥያሜ

ይህ ህገ መንግስት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዲሞክራሲያዊ አወቃቀርን ይደነግጋል። በዚሁ ህግ መሠረት የተቋቋመው መንግስት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሚል ስም ይጠራል።

አንቀፅ 2

የአፋር ብሔራዊ ክልል ወሰን

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት መሠረት የቆመ ሆኖ፥

በሰሜን ምስራቅ _____ ኤርትራ

በሰሜን ምዕራብ _____ ትግራይ ክልል

በደቡብ _____ ኦሮሚያ ክልል

በደቡብ ምዕራብ _____ አማራ ክልል

በደቡብ ምስራቅ _____ ሱማሌ ክልል

በምስራቅ _____ ጂቡቲ ሪፐብሊክ

የሚያዋስኑት መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ያለው ብሔራዊ ክልል ነው።

አንቀፅ 3

ሰንደቅ ዓላማና አርማ

የአፋር ብሔራዊ ክልል የራሱ ሰንደቅ ዓላማና አርማ ይኖረዋል ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀፅ 4

የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር

የአፋር ብሔራዊ ክልል መዝሙር የሕገ መንግስቱን ዓላማዎች፣ የሕዝቡን የጀግንነት ታሪኩን የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲ ስርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲሁም የክልሉ ሕዝብ ባህል እድገትና ብሩህ ተስፋን የሚያንፀባርቅ ሆኖ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀፅ 5

የሥራ ቋንቋ

የክልሉ ብሔራዊ መንግስት የሥራ ቋንቋ አፋርኛ ነው።

አንቀፅ 6

ርዕሰ ከተማ

የክልሉ ርዕሰ ከተማ ሠመራ ነው።

አንቀፅ 7

የፆታ አገላለፅ

በዚህ ሕገ መንግስት ውስጥ ለወንድ ፆታ የተደነገገው የሴቷንም ፆታ ያካትታል።

ምዕራፍ ሁለት

የሕገ መንግስት መሠረታዊ መርሆች

አንቀፅ 8

የሕዝብ ወሳኝነት

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ የአፋር ሕዝብ የብሔራዊ ክልሉ መንግስት የበላይ ስልጣን ባለቤት ነው።
2. የብሔራዊ ክልሉ ሕዝብ የበላይነት የሚገለፀው በሚመርጣቸው ተወካዮችና ራሳቸው በቀጥታ በሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው።

አንቀፅ 9

የሕገ መንግስቱ የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1. ይህ ሕገ መንግስት የብሔራዊ ክልሉ የበላይ ሕግ ነው። ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር እንዲሆም የመንግስት አካል ወይም የባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግስት ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚነት አይኖረውም።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፣ የመንግስት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቻው ይህንን ሕገ መንግስት የማክበርና የማስከበር እንዲሁም ለህገ መንግስቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው።
3. በዚህ ህገ መንግስት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግስትን ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

አንቀፅ 10

ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገሰሱ ናቸው፣
2. በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው።

አንቀፅ 11

የመንግስትና የሃይማኖት መለያየት

1. መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፣
2. መንግስታዊ ሃይማኖት አይኖርም፣
3. መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፣ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

አንቀፅ 12

የመንግስት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ መንግስት አሠራር ለሕዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት።
2. ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳው ይችላል ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
3. ማንኛውም ኃላፊ ወይም የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል።

ምዕራፍ 3

መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

አንቀፅ 13

ተፈፃሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሕግ አውጭ፣ የሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካላት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።
2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት የመሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ድንጋጌዎች ፌዴራላዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰምምነቶች ሰነዶችና መርሆች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ።

ክፍል አንድ

ሰብአዊ መብቶች

አንቀፅ 14

የሕይወት፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት፣

ማንኛውም ሰው ሰብአዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው።

አንቀፅ 15

በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው። ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም።

አንቀፅ 16

የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።

አንቀፅ 17

የነፃነት መብት

1. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ነፃነቱን አያጣም።
2. ማንኛውም ሰው በህግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሠር አይችልም።

አንቀፅ 18

ኢ-ሰብአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ኢሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም። ለማንኛውም አላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው።
3. ማንኛውም ሰው በሃይል ተገዶ ወይም ግዴታ ለማሟላት ማንኛውም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በሃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት የሚለው ሃረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም።

ሀ. ማንኛውም እስረኛ በእስር ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሠራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሠራውን ማንኛውም ሥራ፣

ለ. ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠውን አገልግሎት፣

ሐ. የማሕበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈፀምን ማንኛውም የኢኮኖሚና የማህበራዊ የልማት ሥራ።

አንቀፅ 19

የተያዙ ሰዎች መብት

1. ወንጀል ፈፅመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ምክንያቶቹ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው።
2. የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት ያላቸው ስለመሆኑና ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው።
3. የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው። ይህም ጊዜ ሰዎች ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረቡም በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለፅላቸው መብት አላቸው።
4. የያዛቸው የፖሊስ መኳንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜ ገደቡ መሰረት ፍርድ ቤት በመቅረብ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነታቸን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አላቸው። ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዙት ሰዎች በጥበቃ ሥር እንዲቆዩ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቀድ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለስልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዙት ሰዎች በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ያላቸውን መብት የሚያከብር መሆን አለበት።
5. የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማንኛውም ማስረጃ እንዲያመጡ አይገደዱም በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።
6. የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው። ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች መሠረት ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል።

አንቀፅ 20

የተከሰሱ ሰዎች መብት

1. የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልፅ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው። ሆኖም የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት፣ የሕዝቡን የሞራል ሁኔታና የአገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል።
2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸውና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት አላቸው።
3. ማንኛውም ተከሳሽ በፍርድ ሂደት ባለበት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር፣ በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለው።

4. የተከሰሱት ሰዎች የቀረበባቸውን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማንኛውም ማስረጃ የማቅረብ ወይም እንዲቀርብላቸው የማድረግና ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰማሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።
5. የተከሰሱ ሰዎች በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ የማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግስት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው።
6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጣቸው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው።
7. የፍርዱ ሂደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግስት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጐምላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።

አንቀፅ 21

በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት

1. በጥበቃ ሥራ ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው።
2. ከትዳር ጓደኞቻቸውና ከቅርብ ዘመዶቻቸው ከጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሃኪማቸውና ከሕግ አማካሪያቸው ጋር የመገናኘትና እንዲጐበኙአቸው እድል የማግኘት መብት አላቸው።

አንቀፅ 22

የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙን ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ የአይችልም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈፀመ ጊዜ ለወንጀሉ ተፈፃሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛው ሰው ላይ አይወሰንም።
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 1 ድንጋጌ ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሽ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

አንቀፅ 23

በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ህግና ሥነ ሥርዓት ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጐች መሠረት ተከስሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

አንቀፅ 24

የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛውም ሰው ሰብአዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው፣
2. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሥፍራ በሰብአዊ ፍጡርነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው።
3. ማንኛውም ሰው የራሱን ስብእና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሳደግ መብት አለው።

አንቀፅ 25

የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው። በመካከላቸው ማንኛውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው።

አንቀፅ 26

የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል።
2. ማንኛውም ሰው በግል የሚፅፋቸውና የሚፃፉቸው በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም።
3. የመንግስት ባለስልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው። አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን፣ የሕዝብን ሰላም፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ ለመጠበቅ ወይም

የሌሎችን መብትና ነፃነቶች በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሠረቱ ዝርዝር ሕጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም።

አንቀፅ 27

የሃይማኖት፣ የህሊናና የእምነት ነፃነት

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና የሃይማኖት ነፃነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት መያዝ ወይም የመቀበል ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ የመከተል የመተግበር የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን ያካትታል።
2. በፌዴራል ሕገ መንግስት አንቀፅ 90 ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸውን የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ።
3. ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በሃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም።
4. ወላጆችና ሌሎች ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ስነምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው።
5. ሃይማኖትና እምነትን የመግለፅ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝቡን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ የሌሎች ዜጎች መሰረታዊ መብቶች፣ ነፃነቶችና መንግስት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል።

አንቀፅ 28

በስብዕና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የሀገሪቱ ሕጎች በሰው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች በተለይ የሰው ዘር ማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙት ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በሕግ አውጭው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግስት አካል ውሳኔዎች በምህረት በይቅርታ አይታለፍም።

ክፍል ሁለት

ዲሞክራሲያዊ መብቶች

አንቀፅ 29

የአመለካከት፣ ሀሳብ በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል።
2. ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሃሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት በአገር ውስጥም ሆነ በአገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት፣ በስነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውም አይነት መረጃና ሃሳብን የመሰብሰብ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል።
3. የኘሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። የኘሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፡
    a. የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑ፣
    b. የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት
4. ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሃሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ኘሬስ በተቋምነቱ የአሰራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግበታል።
5. በክልሉ ውስጥ በመንግስት ገንዘብ የሚካሄደው ወይም በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።
6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ህጋዊ ገደቦች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናል።
7. ማንኛውም ሰው ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦች ጥሰ ከተገኘ በህግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።

አንቀፅ 30

የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅብ መብት አለው።ከቤት ውጪ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን ዲሞክራሲያዊ መብቶችና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ስርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ።

2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ህጐች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።

አንቀፅ 31

የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ህግ ለመጣስ ወይም ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በህገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጊቶች የተከለከሉ ይሆናሉ።

አንቀፅ 32

የመዘዋወር ነፃነትና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት መብት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በህጋዊ መንገድ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው በመረጠው የክልሉ አካባቢ የመዘዋወርና መኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ ሰርቶ የመኖር፣ ሀብት ንብረት የማፍራት፣ የመሸጥ፣ የማስተላለፍ፣ የማውረስ እና የመያዝ እንዲሁም በፈለገ ጊዜ ከክልሉ የመውጣት መብት አለው።

አንቀፅ 33

የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በሃይማኖት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው። በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው። በፍችም ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ።
2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ይመሰረታል።
3. ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው። ከሕብረተሰቡና ከመንግስት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።
4. በባህል በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሥርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል።
5. ይህ ሕገ መንግስት የግል የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖታዊ በባህላዊ ሥርዓት መሠረት መዳኘትን አይከለክልም። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

አንቀፅ 34

የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ሕገ መንግስት በአረጋገጠላቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።
2. ሴቶች በዚህ ሕገ መንግስት በተደነገገው መሠረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።
3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት ሲታዩ በመቆየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን የታሪክ ጠባሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ጠባሳ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው። ከዚህም አኳያ የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግስትና በግል ተቋማት ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው።
4. ሴቶች ከጉጂ ልማደዊ ድርጊቶች ተፅዕኖ ለመላቀቅ ያላቸውን መብት መንግስት ማስከበር አለበት። ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው።
5. ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ እድገት፣ እኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው።

    ሀ.. የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያጋር የማግኘት መብት አላቸው። የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሠራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት፣ የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል።

    ለ. የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሠረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል።

    ሐ. ሴቶች በእርገዝና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳይ ለመከላከልና ጤንነታቸው ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው።

    መ. ሴቶች ንብረት የማፍራት የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው። በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ በማስተዳደርና በመቆጣጠ ረገድ ከወንዶች እኩል መብት አላቸው። እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው።

    ሠ. ሴቶች በብሔራዊ ክልሉ የልማት ፖሊሲዎች እቅድና በኘሮጀክቶች ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ኘሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።

አንቀፅ 35

የሕግናት መብት

1. ማንኛውም ሕግን የሚከተሉት መብቶች አሉት።

ሀ. በህይወት የመኖር፣

ለ. ስምና ዜግነት የማግኘት፣

ሐ. ወላጆቹን ወይም በህግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

መ. ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርት፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎችን እንዲሰራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣

ሠ. በትምህርት ቤቶች ወይም በሕግናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን፣

2. ሕግናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጐት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች፣ ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕግናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት።
3. ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋማት የሚገኙ በመንግስት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች በመንግስት ወይም የግል እንለማውተን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው።
4. ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱ ሕግናት በጋብቻ ውስጥ ከተወለዱ ሕግናት ጋር እኩል መብት አላቸው።
5. መንግስት ለእንለማውታኑ ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል።

አንቀፅ 36

ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከተው ውሳኔ ወይም ፍርድ፣

    ሀ. ማንኛውም ማህበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል

ለ. ማንኛውም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

አንቀፅ 37

የአፋር ሕዝብ የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት

የአፋር ሕዝብ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው። በዚህ መሠረት የአፋር ሕዝብ፡

1. የራሱን ብሐራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብና የማበልፀግ የማሳደግ፣ ባህሉንና ቋንቋውን የመግለፅ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አለው።
2. በራስ መልከዓ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራስን ጉዳይ በራስ የመጨረስ፣ በራስ የማስተዳደርና እንዲሁም በፌዴራላዊ መንግስት ውስጥ በነፃነት፣ ተገቢና ፍትሀዊ የሆነ የውክልና አግባብ ውጤታማ ተሳትፎ ለማድረግ መብት አለው።
3. የአፋር ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር መብት፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልከዓምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግስታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል መንግስት አስተዳደር ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል።
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እስከ አንቀፅ 3 የተጠቀሱት መብቶች ታገዱ፣ ተረገጡ፣ ወይም ተሸራረፉብኝ ብሎ ባመነበትና ባንድነት ስር ሆኖ ሊያስተካክላቸው ባልቻለበት ጊዜ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 39 በተደነገገው መሠረት የራስን እድል በራስ እስከ መገንጠል ድረስ የመወሰን መብቱን ተግባራዊ ያደርጋል።
5. የአፋር ሕዝብ የራሱን እድል የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያለ መብት በሥራ ላይ የሚውለው፡-

    ሀ. የመገንጠል ጥያቄ በሕግ አውጭ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ የድምፅ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲያረጋግጥ፣

    ለ. የፌዴራሉ መንግስት የሕዝብ ምክር ቤቱ የመገንጠል ውሳኔ በደረሰው በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሕዝብ ውሳኔ እንዲካሄድ ሲያደርግ፣

    ሐ. የመገንጠል ጥያቄ በሕዝብ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ፣

    መ. የፌዴራሉ መንግስት መገንጠሉን ለመረጠው የአፋር ብሐራዊ ክልል ምክር ቤት ስልጣኑን ሲያስረክብ

    ሠ. በሕግ በሚወሰነው መሠረት በፌዴራሉ መንግስትና ለመገንጠል የወሰነው የአፋር ብሐራዊ ክልል መንግስት መካከል የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው።

6. በዚህ ሕገ መንግስት ውስጥ የአፋር ሕዝብ ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያለው፣ የአፋርኛ ቋንቋ የሚናገር፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለኝ ብሎ የሚያምንና በአብዛኛው በተያያዘ መልከአ ምድር የሚኖር ሕብረተሰብ ነው።

አንቀፅ 38

የንብረት መብት

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል፣ ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ ለሌላ ሁኔታ በሕግ አስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም፣ ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረኑ ድረስ ንብረት የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም ለሌላ ወገን የማስተላለፍ መብቶች ያካትታል።
2. በዚህ አንቀፅ ዓላማ የግል ንብረት ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው አገር አቀፋዊ ወይም ክልላዊ ማህበራት፣ ወይም አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤቶች፣ እንዲሆኑ በተፈቀደላቸው ማህበረሰቦች በፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው።
3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የክልሉ ህዝብ የጋራ ንብረት ነው።
4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
5. በክልሉ የሚገኙ አርብቶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት ያስከብርላቸዋል ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
6. የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግስት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል።ዝርዝሩም በሕግ ይወሰናል።
7. ማንኛውም ሰው በጉልበቱ ወይም በገንዘብ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቀሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል ዝርዝር አፈፃፀሙ በሕግ ይወሰናል።
8. የግል ንብረት ባለቤትነት መበት እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረቱን ለመወሰድ ይችላል።

አንቀፅ 39

የኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች

1. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪና በክልሉ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው።

3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግስት ገንዘብ በሚካሄደው ማህበራዊ አገልግሎት በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው።
4. የክልሉ መንግስት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመደባል።
5. የክልሉ መንግስት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል።
6. የክልሉ መንግስት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል። እንዲሁም በሚካሄደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ እድል ለመፍጠር የሥራ ንርግራሞችን ያወጣል ንርጀክቶችን ያካሂዳል።
7. የክልሉ መንግስት የክልሉ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ሥራ የማግኘት እድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።
8. የአርብቶ አደሮችና ገበሬዎች በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውንና ለብሔራዊ ሃብት ካደረጉት የምርት አስተዋፅኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት አላቸው። መንግስት የኢኮኖሚ ማህበራዊና የልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት።
9. የክልሉ መንግስት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለስነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋፅኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።
10. የክልሉ አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች የብድር አገለግሎት እንዲሁም ለእንስሳት እርባታና ግብአቶች ያመች ዘንድ መንገድ፣ ገበያና ሌሎች መሠረተ ልማቶች እንዲዘረጉ ልዩ ጥረት ያደርጋል።

አንቀፅ 40

የሠራተኛ መብት

1. የፋብሪካና አስተዳደር ሠራተኞች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ገበሬዎች ሌሎች የገጠር ሠራተኞች ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግስት ሠራተኞች

    ሀ. የሥራና የኢኮኖሚ ሆኔታዎችን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው። ይህ መብት የሠራተኛ ማህበራትንና ሌሎች ማህበራትን የማደራጀት ከአሰሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል።

    ለ. በንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ የማቆምን ጨመሮ ቅሬታ የማሰማት መብት አላቸው።

    ሐ. በንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ እና /ለ/ መሠረት እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉ የመንግስት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ።

    መ. ከወንዶች ጋር እኩል ሥራ የሠሩ ሴት ሠራተኞች ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብት አላቸው።

2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ እረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስየሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።
3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እውቅና ያገኙት መብቶች ሳይቀነሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነገጋል።

አንቀፅ 41

የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታዎችን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።
2. የክልሉ ነዋሪዎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ በሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ኘሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።
3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት ይሆናል።

አንቀፅ 42

የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው።
2. የክልሉ መንግስት በሚያካሂዳቸው ኘሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግስት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማሻሻያ የማግኘት መብት አላቸው።

ምዕራፍ አራት

የክለሉ መንግስት አደረጃጀትና የስልጣን ክፍፍል

አንቀፅ 43

የክልሉ የአስተዳደር እርከኖች

1. ክልሉ በከተማ በቀበሌ፣ በወረዳና በክልል ምክር ቤት የተዋቀረ ነው። ይሁን እንጂ የክልሉ ም/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር እርከኖች ሊያዋቅርና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን ይችላል።
2. የክልሉ ነዋሪ የሆነው የአርጎባ ሕዝብ የልዩ ወረዳ ውክልና በዚህ ህገ መንግስት ተረጋግጧል።

አንቀፅ 44

የክልሉ መንግስት የሥልጣን አካላት

1. የክልሉ መንግስት ህግ አውጪ አካል የክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱ ለወከለው ህዝብ ነው።
2. የክልሉ ከፍተኛ የህግ አስፈፃሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የክልል የዳኝነት ስልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

አንቀፅ 45

የክልሉ መንግስት ስልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ውስጥ በግልጽ ተለይተው ለፌዴራሉ መንግስት ወይም ለፌዴራሉ መንግስትና ለክልሉ መንግስት በጋራ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ውጭ ያለ ማንኛውም ስልጣንና ተግባር የክልሉ መንግስት ተግባር ይሆናል።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የሰፈረው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ክልላዊ መንግስቱ፡-

   ሀ. የክልሉን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እቅድ ያወጣል ያስፈጽማል።

   ለ. የክልሉን ህገ መንግስትና ሌሎች ህጐችን ያወጣል ያስፈፅማል።

   ሐ. የፌዴራሉ መንግስት በሚያወጣው ህግ መሠረት መሬትንና የተፈጥሮ ሃብትን ያስተዳድራል።

   መ. ራስን በራስ ማስተዳደር ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል፣ የህግ የበላይነት የሠፈነበትን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስትና ይህንን ህገ መንግስት ይጠብቃል፣ ይከታተላል።

   ሠ. በክልሉ ውስጥ መሠረታዊ የእንስሳት ሀብት ልማትና ግጦሽ ልማት በአጠቃላይ በግብርና ልማት ሥራዎች ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ስራዎቹ በአግባቡ መከናወናቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።

   ረ. የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ህግ ያወጣል ያስፈጽማል፣ ይህን በማያስፈጽምበት ጊዜ የህገሪቱን የትምህርት የስልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

ሰ. የክልሉን ፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል።

ሸ. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 28 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በህግ መሠረት ምህረት ወይም ይቅርታ ያደርጋል።

ቀ. ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶች ይጥላላ፣ ይሰበስባል። የክልሉን በጀት ያዘጋጃል ያፀድቃል ያስተዳድራል።

በ. በክልል መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የስራ ግብር ይጥላል ይሰበስባል።

ተ. የመሬት መጠቀሚያ ክፍያን ይወስናል ይሰበስቦል።

ቸ. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል ይሰበስባል።

ነ. በክልሉ በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል።

ኘ. በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በህጉ መሠረት ይሰበስባል።

ኀ. ከፌዴራል መንግስትጋር

1. በጋራ ከሚያቋቁማቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር የሥራ ግብር የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በህጉ መሠረት ይካፈላል።
2. ከድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ ከባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በህጉ መሠረት ይካፈላል።
3. ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማንኛውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በህጉ መሠረት ይካፈላል።

አ. በክልል መስተዳድሩ አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል ይሰበስባል።

ከ. ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያን ይወስናል።

ወ. በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ በስራ ላይ ያውላላ።

ምዕራፍ አምስት

ስለ ክልሉ ም/ቤት

አንቀፅ 46

ስለ ክልሉ ም/ቤት አባላት

1. የክልሉ ምክር ቤት አባላት ነፃ ቀጥተኛ ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚሰጥር በሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ።
2. የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
3. የምክር ቤቱ አባላት የመላው የክልሉ ህዝብ ተወካዮች ናቸው። ተገዥነታቸውም

ሀ. ለህገ መንግስቱ

ለ. ለመረጣቸው ህዝብና

ሐ. ለህሊናቸው ብቻ ይሆናል።

1. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምፅ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም አስተዳደራዊ እርምጃ አይወሰድበትም።
2. ማንኛውም የክልል ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም በወንጀል አይከሰስም።
3. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ህዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በህጉ መሰረት ከምክር ቤት አባልነት ይወገዳል።

አንቀፅ 47

የክልሉ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ምክር ቤት በዚህ ህገ መንግስት መሰረት የክልሉ ህግ አውጪ አካል ነው።
2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በብሔራዊ ክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነው።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ስር የሰፈረው አጠቃላይ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ም/ቤቱ በተለይ የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

ሀ. በዚህ ህገ መንግስት መሰረት የፌዴራሉን ህገ መንግስትና ሌሎች ህጐችን የማይፃረሩ ልዩ ልዩ ህጐች ያወጣል።

ለ. የሕዝብን ብዛት የክልሉን ስፋትና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ግምት ውስጥ በማስገባት በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነው።

ሐ. የፌዴራሉ መንግስት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጐራባች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጋር የሚደረጉ ስምምነቶችን ያፀድቃል።

መ. የራሱ አፈጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ ይመርጣል፣ ለምክር ቤቱ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ይሰይማል።

ሠ. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ርዕሰ መስተዳድሩን ይሰይማል፣ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን ምክትል ርዕሰ መስተዳድርና የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያፀድቃል።

ረ. በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ኘሬዝዳንት፣ ምክትል ኘሬዝዳንት፣ ዋና ኦዲተሩንና ምክትል ዋና ኦዲተሩን ይሾማል።

ሰ. የክልል፣ የዞንና የወረዳ የዳኝነት አካላትን ያቋቁማል።

ሸ. የኦዲትና የቁጥጥር አካላትን ያቋቁማል።

ቀ. በህጉ መሰረት ምህረት ያደርጋል።

በ. የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ያወጣል የፀጥታና የፖሊስ ሃይሉን ያቋቁማል።

ተ. የብሔራዊ ክልሉን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኘሮግራሞች ያፀድቃል።

ቸ. የብሔራዊ ክልሉን የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ህጉች ያወጣል፣ የክልሉን በጀት መርምሮ ያፀድቃል።

ነ. ለማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት ለኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠንና ለዲሞክራሲያዊ ስልጣን ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን ያቋቁማል።

ኘ. ለክልሉ መንግስት በተከለለው የገቢ ምንጭ በክልሉ ውስጥ ግብርና ታክስ ይጥላል።

አ. የክልል መስተዳድሩን የሠራተኛ አስተዳደር የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ህግ ያወጣል።

ከ. በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ 45 ንዑስ አንቀፅ 2 (ወ) ሥር ለክልሉ መንግስት በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል።

ወ. በተለይ በግብርና ልማት ስር የእንስሳት ሀብት ልማትና የግጦሽ ልማት ወዘተ የሥራ እንቅስቃሴዎች በመስተዳድር ምክር ቤት እና በቀጥታ ጉዳዩ በሚመለከተው አስፈፃሚ አካል እየተከናወኑ መሆናቸውን ይከታተላል።

ጎ. የህገሪቱንና የክልሉን ህግጋት መንግስታት፣ አዋጆችና ሌሎች ህጉችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ደንቦችን ያወጣል።

ወ. የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግስት ባለስልጣናት ለጥያቄ ይጠራል። የአስፈፃሚውን አካል አሠራር ይመረምራል።

አንቀፅ 48

ስለ ክልሉ ምክር ቤት

የክልሉ ምክር ቤት የራሱ ፅህፈት ቤት ይኖረዋል።

የፅህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል።

አንቀፅ 49

ስለ ምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ 47 ንዑስ 3(መ) መሠረት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየም ሆኖ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
2. የአፈ-ጉባኤ የሥራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

አንቀፅ 50

የአፈ-ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

የክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ በዚህ ህገ መንግስት መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል።

1. የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል ይመራል።
2. ምክር ቤቱን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል።
3. የምክር ቤቱን ፅህፈት ያደራጃል፣ ጠቅላላ የአስተዳደር ስራዎችን በበላይነት ይመራል።
4. ምክር ቤቱ በአባሎች ላይ እንዲወሰድ የወሰነውን የዲሲፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል።
5. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀፅ 51

የምክትል አፈ-ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

ምክትል አፈ-ጉባኤ ተጠሪነቱ ለአፈ-ጉባኤውና ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ።

1. በአፈ-ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
2. አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

አንቀፅ 52

የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የክልሉ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ከሁለት ሶስተኛው በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ስብሰባው ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፣ የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት አብላጫ ድምፅ ይተላለፋል።
3. የክልሉ ምክር ቤት አባላት የማመረጡት ለአመስት ዓመታት ነው የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ አንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።
4. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በሚያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛው በላይ የሚሆኑ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ በጠየቁ ጊዜ አፈ-ጉባኤው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።
5. የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል። ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ወይም በክልሉ አስፈፃሚ አካል በተጠየቀና በምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ ላይ የሚሆኑ ጥያቄውን ከደገፉ ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

አንቀፅ 53

የምክር ቤቱ ውሳኔዎችና የአሰራር ሥነ ሥርዓቶች

1. በዚህ ህገ መንግስት ውስጥ ተገልፆ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በምክር ቤቱ አባላት አብላጫ ድምፅ ይሆናል።
2. ምክር ቤቱ ውስጣዊ አሰራሩንና የህግ አወጣጡን ሂደት አስመልክቶ ዝርዝር ደንቦችን ሊያወጣና በሥራ ላይ ላይ ሊያውል ይችላል።

አንቀፅ 54

የአስፈፃሚነት ስልጣን

1. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ የአስፈፃሚ ስልጣን የተሰጠው ለርዕሰ መስተዳድሩና ለመስተዳድር ምክር ቤት ነው።
2. ርዕሰ መስተዳድርና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነታቸው ለብሄራዊ ክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት በመንግስት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

ለአንቀፅ 55

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አወቃቀር

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድር፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፣ የአስፈፃሚ ቢሮዎች ኃላፊዎችና በህግ በሚወሰነው መሠረት ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነው።
2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ርዕሰ መስተዳድሩ ናቸው።
3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ነው።
4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወሰነው ውሳኔ ለክልሉ ም/ቤት ተጠሪ ይሆናሉ።

አንቀፅ 56

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

የፌዴራሉ ህገ መንግስት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በክልሉ ምክር ቤትና በፌዴራሉ መንግስት የወጡ ህጐችና የተላለፉ ውሳኔዎች በክልሉ ውስጥ በስራ መተርጐማቸውን ያረጋግጣል።
2. የክልሉ ም/ቤት የአስፈፃሚ አካላትና ሌሎች ተቋማት አደረጃጀት ይወስናል። ስራቸውን ይከታተላል በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል።
3. የክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ይነድፋል፣ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል የተወሰነውንም ያስፈጽማል።
4. በክልሉ ውስጥ ህግና ስርዓት መከበሩን ያረጋግጣል በህግ መሠረት ይቅርታ ያደርጋል።
5. የክልሉ ም/ቤት በሚሰጠው ስልጣን መሠረት ደንቦችና መመሪያዎች ያወጣል።
6. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ረቂቅ አዘጋጅቶ ለክልል ምክር ቤት ያቀርባል።

7. በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ 45 ንዑስ አንቀፅ 2 (ወ) ሥር ለክልል ምክር ቤት አስቀድሞ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ ሊሰበብ ባልቻለበት ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል።
8. የክልሉ አርብቶ አደር የኑሮ ሁኔታ የተሻለና ከኋላ ቀር አሰራር የሚላቀቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል።
9. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

አንቀፅ 58

የርዕሰ መስተዳድሩ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. ርዕሰ መስተዳድር በክልሉ ምክር ቤት ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል።
2. በዚህ ህገ መንግስት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የርዕሰ መስተዳድሩ የስራ ዘመን የብሔራዊ ክልል ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ነው።

አንቀፅ 59

የርዕሰ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባር

1. ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ መስተዳድር የሥራ መሪ፣ የመስተዳድር ምክር ቤቱ ሰብሳቢና የብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ነው።
2. ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለክለሉ ምክር ቤት ነው።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ

ሀ. የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል።

ለ. የክልሉ መንግስት ህግ አውጪና ህግ አስፈፃሚ አካላት በየበኩላቸው መክረው ያፀደቁዋቸውን አዋጆችና ደንቦች በአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ይታወጁ ዘንድ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ፊርሞ ይልካል።

ሐ. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈፃሚነት ይከታተላል።

መ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዝዳንት ምክትል ኘሬዝዳንት የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተርን መርጦ ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል።

ሠ. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን የዞን አስተዳዳሪዎችንና የመስተዳድር ም/ቤት አባላት የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎችን ሹመት ለክልል ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል።

ረ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ፊደል ተራ ቁጥር መ እና ሠ ሥር የሰፈረው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜና ሁናቴ ከምክትል ርዕሰ መስተዳድሩና የዞን አስተዳደሪዎች በመለስ ያሉትንና ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የሥራ ኃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሰራል።

ሰ. ከክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ውጭ የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎች ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች፣ ኮሚሽነሮች መምሪያ ኃላፊዎችና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎችን መርጦ ይሾማል።

ሸ. የብሔራዊ ክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል።

ቀ. በክልሉ የሚገኙትን የበታች የአስተዳደር እርከኖች ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል።

በ. በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

ተ. ዝርዝሩ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ሆኖ አስፈላጊነታቸው እየታየ በተመረጡ ስፍራዎች የክልል አስተዳድሩን የሚወክሉና ለወረዳዎች ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚሰጡ የአስተዳደር አካባቢ ተጠሪ ጽሕፈት ቤቶች ያቋቁማል። የአስተዳዳሪዎችንና ሌሎች ስራ ኃላፊዎችን ይሰይማል።

አንቀፅ 60

የምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባር

1. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ከብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት መካከል በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በብሔራዊ ክልሉ ምክር ቤት የሚሾም ሆኖ የሚከተሉት ስለጣንና ተግባራት የኖሩታል።

ሀ. በርዕሰ መስተዳድሩና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናለ።

ለ. ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

2. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነው።

አንቀፅ 61

የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት

1. ርዕሰ መስተዳድሩ በህገ መንግስቱ የተሰጠውን ስልጣን ለመወጣት ያስችለው ዘንድ የራሱ የሆነ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።
2. የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት የመስተዳድሩ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል።

3. የጽሕፈት ቤቱ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በህግ ይወሰናል።

አንቀፅ 62

ስለ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ አስተዳደራዊ ተቋማት መቋቋም

1. የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ የእለት ተእለት ሥራዎች የሚያከናውኑ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ልዩ ልዩ ቢሮዎችና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ተቋማት እንደአስፈላጊነታቸው ይቋቋማሉ።
2. የቢሮዎችና ሌሎች ከፍተኛ ተቋማት ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ለመስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ያልሆኑ ቢሮዎችና ሌሎች ተቋማት ተጠሪነት ከተቋቋሙበት አላማና ከሚያስፈጽሙ ተልዕኮ ጋር አግባብነት ላላቸው የክልሉ መንግስት የበላይ አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ይሆናል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀፅ 63

የሽማግሌዎች ጉባኤ ስለማቋቋም

የክልሉ ምክር ቤት እንደ አስፈላጊነቱ የአገር ሽማግሌዎች ጉባኤ በተለያየ እርከን ያቋቁማል ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

ምዕራፍ ሰባት

ስለ ፍርድ ቤት አወቃቀርና የዳኝነት ስልጣን

አንቀፅ 64

ስለነፃ የዳኝነት አካል መቋቋም

1. የክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ህገ መንግስት ተቋቁሟል።
2. የዳኝነት ስልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በህግ የመዳኘት ስልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጭ የሚደረግና በህግ የተደነገገውን የዳኝነት ሥርዓት የሚከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት ይቋቋማል።

አንቀፅ 65

ስለባህላዊና ሃይማኖታዊ የዳኝነት አካል

በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ 64 ንዑስ አንቀፅ 2 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ህገ መንግስት ከመፅደቁ በፊት ከመንግስት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካል በዚህ ህገ መንግስት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

አንቀፅ 66

የዳኝነት ስልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው።
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል፣ ከማናቸውም የመንግስት አካል ባለስልጣን ወይም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው።
3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ በነፃነት ያከናውናሉ፣ ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።
4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በህግ የተወሰነው የጡረታ እድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ስራው አይነሳም።

ሀ. የዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲሲፒሊን ህግ መሰረት ጥፋት ፈፅሟል ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ወይንም በህመም ምክንያት የዳኝነት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲያምንና

ለ. የጉባኤው ውሳኔ ለክልሉ ምበክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ የአብላጫ ድምፅ ሲደገፍና ሲፀድቅ

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት አንድ ዳኛ ከዳኝነት ስራው የሚያስነሳው ጥፋት ፈፅሟል ብሎ ጉባኤው ከወሰነበት ጉዳዩ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ እስኪታይ ድረስ ከዳኝነት ስራው ታግዶ መቆየት ይኖርበታል።
6. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም።

አንቀፅ 67

የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ስልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና፣ በወረዳ ፍርድ ቤቶች ይደራጃል። የወረዳ ፍርድ ቤት የክልሉ የበታችና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነው።
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

ሀ. ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ስልጣን፣

ለ. በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራሉ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን፣

ሐ. ማናቸውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የወሰነውን የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካለው ክልላዊ ስልጣን በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሆን ይዳኛል።
4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል።
5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል።
6. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።
7. የክልሉ ፍርድ ቤቶች በውክልና የሚፈፅሙትን ፌዴራላዊ ዳኝነት ተግባር ለማከናወን የሚያወጡትን ገንዘብ ወጪ በተመለከተ ከፌዴራል መንግስት ማካካሻ እንዲሰጣቸው የክልሉ ጠቅላይ ፈርድ ቤት ኘሬዝዳንት ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀርባል።

አንቀፅ 68

ስለ ዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዝዳንትና ምክትል ኘሬዝዳንት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞችና የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።
3. የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በእጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልል ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። ሆኖም የፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተጠየቀውን አስተያየት በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የእጩ ዳኞችን ሹመት ያፀድቃል።

አንቀፅ 69

ስለ ክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምፅ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይቋቋማል።
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዝዳንት ጉባኤውን በሊቀመንበርነት ይመራል።

3. የጉባኤ አባላት ዝርዝር ስብጥር ስልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል።

አንቀፅ 70

ህገ መንግስቱን ስለመተርጎም

1. በክልሉ ውስጥ የህገ መንግስታዊ ክርክር ጉዳይ ወይም የትርጉም ጥያቄ ሲነሳ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የወረዳ ምክር ቤቶች የተመረጡ አንዳንድ አባላት ተወጣጥቶ በሚሰየም የህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሽን በዚህ ህገ መንግስት ተቋቁሟል።
2. ኮሚሽኑ የክልሉ ህገ መንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ህገ መንግስታዊ ጉዳዮች ላይ መክሮ በስልሳ (60) ቀናት ውሳኔ ይሰጣል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የተቋቋመው ኮሚሽን አገልግሎት ዘመን አምስት ዓመት ሲሆን ህገ መንግስታዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ይሰበሰባል።
4. ኮሚሽኑ የራሱ ሰብሳቢና ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል መርጦ ስራውን የሚያከናውን ሲሆን ለሥራው የሚያስፈልገው የጽህፈት ቤት አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ ከክልሉ ምክር ቤት ያገኛል።

አንቀፅ 71

የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

1. የክልሉ ህገ መንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ህገ መንግስት ተቋቁሟል።
2. የክልሉ መንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አስራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዝዳንት ሰብሳቢ

ለ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ኘሬዝዳንት ምክትል ሰብሳቢ

ሐ. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በብሔራዊ ክልል ምክር ቤት የሚሾሙና በሙያ ብቃታቸውና በስነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የህግ ባለሙያዎች አባላት።

መ. በአፈ-ጉባኤው አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ በሚሰየሙ ሶስት ተወካዮች አባላት።

አንቀፅ 72

የአጣሪ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ይህንን ህገ መንግስት መሠረት አድርጎ ከብሔራዊ ክልሉ የሚመነጩ ህገ መንግስታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ስልጣን ይኖረዋል። በሚደረገው ማጣራት መሰረትም የክልሉን ህገ መንግስት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳዮ ላይ የራሱን የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሽን ያቀርባል።
2. አጣሪው ጉባኤ በክልሉ መንግስት አባላት የሚወጡ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ ህገ መንግስት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በማናቸውም ሁኔታ ሊነሳና ጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች አማካኝነት ሲቀርብለት ከመረመረና ካጣራ በኋላ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኮሚሽኑ ያቀርባል።
3. በፍርድ ቤቶች ዘንድ የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ አጣሪ ጉባኤው፡-

ሀ. የክልሉን ህገ መንግስት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይመልሳል። ሆኖም ባጣሪ ጉባኤው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ባለጉዳይ ይህንኑ ቅሬታውን በፅሁፍ አዘጋጅቶ ለኮሚሽን በይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

ለ. የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ህገ መንግስታዊ ትርጉም አሰናድቶ ለኮሚሽኑ ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል።

ምዕራፍ ስምንት

ስለወረዳ መስተዳድር አደረጃጀት እና ስልጣን

አንቀፅ 73

አደረጃጀት እና አሠራር

የወረዳ መስተዳድር ከአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በታች የሚደራጅ የመንግስት አስተዳደር መዋቅር ሆኖ የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል።

1. በስሩ ከተደራጁት ቀበሌዎች በሚወከሉ የሕዝብ ተመራጮች ተዋጽኦ የሚቋቋም የወረዳ ምክር ቤት
2. ከዚህ ምክር ቤት አባላት መካከል ተመርጦ በሚሰየም የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አማካኝነት የሚቋቋም የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት

3. በዚህ ሕገ መንግስት መሠረት የተቋቋመ የወረዳ የዳኝነት አካል

አንቀፅ 74

የወረዳ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳ መስተዳድር በተደራጀበት አካባቢ የኢኮኖሚያዊ ልማትና ማሕበራዊ አገልግሎት እቅዶችን ለማዘጋጀትና የሚያወጧቸውን ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ማናቸውም ስልጣን ይኖረዋል።
2. እያንዳንዱ ወረዳ እራሱን የማስተዳደር፣ አካባቢውን የማልማትና በውስጣዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠት መብትና ስልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከክልል ምክር ቤት ቀጥሎ የሚገኝ የበታች አካል ነው።

አንቀፅ 75

ስለወረዳ ምክር ቤት አባላት አመራረጥ እና ተጠሪነት

1. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ወረዳው በተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣሉ።
2. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነታቸው ለመረጣቸው ሕዝብ ይሆናል።

አንቀፅ 76

የወረዳ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳ ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ውስጥ ከፍተኛው መንግስታዊ የስልጣን አካል ነው። ተጠሪነቱም ለክልል ምክር ቤት ይሆናል።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ ስር የሠፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣን እና ተግባር ይኖሩታል።

ሀ. የወረዳውን ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ አስተዳደራዊ የሥራ እቅዶችና ኘሮግራሞች ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል።

ለ. በወረዳው ውስጥ መሠረታዊ የእንስሳት ሀብት ልማት እና የግጦሽ ልማት በአጠቃላይ የግብርና ልማት ስራዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሄዳቸውንና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ አንክብካቤ ሥራ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መከናወኑን ይከታተላል።

ሐ. ነዋሪው ሕዝብ ለልማት ስራ በስፋት የሚነሳሳበትንና የሚንቀሳቀስበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል።

መ. ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ሆኖ ከምክር ቤት አባላት መካከል አፈ-ጉባኤውን ምክትል አፈ-ጉባኤውንና ዋና አስተዳዳሪውን በምርጫ ይሰይማል። በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪና የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ተቀብሎ ያፀድቃል።

ሠ. የራሱን ውስጣዊ የአሰራር ስነ ስርዓት መመሪያ ያወጣል።

ረ. ዝርዝሩ በህግ የሚወሰን ሆኖ የመሬት መጠቀሚያታክስና የእርሻ ስራ ገቢ ግብርና ሌሎች ገቢዎች መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል። ሌሎች የአገልግሎት ታክሶችንና ክፍያዎችን ይጠቀማል።

ሰ. የራሱን በጀት መርምሮ ያፀድቃል ክልሉ ከሚመድበውና ከሚያስተዳድረው ውጭ ያለውንና የወረዳውን የገቢ ምንጭ ይጠቀማል።

ሸ. የፌዴራልና የክልሉን ህግጋት መንግስታትና ሌሎች ህጐች እንደተጠበቁ ሆነው የወረዳውን ሰላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ አውጥቶ በስራ ላይ ያውላል።

ቀ. የወረዳውን ዋና አስተዳዳሪ ጨምሮ ሌሎች የወረዳውን ባለስልጣናት ለጥያቄ ይጠራል። የአስፈፃሚውን አካል አሰራር ይመረምራል።

አንቀፅ 77

ስለምክር ቤቱ አመራር

የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት እንደኖረው ሆኖ ከአባላቱ መካከል ተመርጠው በሚሰየሙ አንድ አፈ-ጉባኤና አንድ ምክትል አፈ-ጉባኤ ይመራል።ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

አንቀፅ 78

ስለ ወረዳ አፈ-ጉባኤ ስልጣን

1. አፈ-ጉባኤው ተጠሪነቱ ለወረዳው ምክር ቤት ሆኖ
2. ወቅቱን ጠብቆ ምክር ቤቱን ለስብሰባ የመጥራትና ጉባኤውን የመምራት ኃላፊነት ይኖርበታል።

3. ሌሎች የአፈ-ጉባኤው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች የክልል ምክር ቤቱን አፈ-ጉባኤ አስመልክቶ በዚህ ሕገ መንግስት የተደነገጉት እንደየአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀፅ 79

ስለ ወረዳ ምክትል አፈ-ጉባኤ ስልጣን

ምክትል አፈ-ጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈ-ጉባኤውና ለወረዳ ምክር ቤት ሆኖ

1. በአፈ-ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
2. አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይቻልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።

አንቀፅ 80

የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜ እና የሥራ ዘመን

1. የወረዳ ምክር ቤት በየሶስት ወሩ ይሰበሰባል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ሁለት ሶስተኛው (2/3) በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣ የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት አብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።
3. የወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል የምክር ቤት የስራ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።
4. የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ-ጉባኤው የምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

አንቀፅ 81

ስለ ወረዳ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት

የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ጽህፈት ቤት ሊኖረው ይችላል።

ሆኖም ምክር ቤቱ የራሱን ጽህፈት ቤት አስኪያደራጅ ድረስ የመስተዳድር ምክር ቤቱንና የዋና አስተዳዳሪውን ጽህፈት ቤት እና የቢሮ መገልገያዎች በመጋራት ይሠራል።

አንቀፅ 82

ስለ ወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት

1. የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ከፍተኛ ሕግ አስፈፃሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለዋና አስተዳደሪውና ለወረዳው ምክር ቤት ነው።
2. የወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት የወረዳው አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪ፣ እንዲሁም በወረዳው ውስጥ የተቋቋሙ ዋና ዋና አስፈፃሚ የሴክተር ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች የሚገኙበት አካል ሆኖ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪው ይሆናል።

አንቀፅ 83

ስለወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ. የፌዴራሉና የክልሉ መንግስታት ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ እቅዶችና ፕሮግራሞች በተቋቋሙበት ወረዳ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

ለ. በወረዳው ውስጥ ያሉ አስፈፃሚ አካላትን በበላይነት ያስተባብራል ሥራቸውን ይከታተላል ይመራል።

ሐ. የወረዳውን አመታዊ በጀት ረቂቅ ያዘጋጀል፣ ለምክር ቤቱ ያቀርባል ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል።

መ. የወረዳውን ሰላምና ፀጥታ ይጠብቃል፣ የወረዳውን ፀጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል ሥራቸውን ያስተባብራል።

ሠ. የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል። ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

ረ. የተፈጥሮ ሃብትን ይጠብቃል፣ ያለማል፣ ይንከባከባል ሕዝቡን ለልማት ስራ በስፋት ያነሳሳል።

ሰ. በወረዳው ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ቅርሳ ቅርስ አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት ስለመሆኑ በቅርበት ይከታተላል።

ሸ. በወረዳው ያሉ አርብቶ አደሮች የኑሮ እንቅስቃሴን ይከታተላል፣ በእንስሳት ሀብት በግጦሽ ልማት እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል ይቆጣጠራል።

ቀ. በህጉ መሠረት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር እና ሌሎች ገቢዎችን ይሰበስባል ተጨማሪ ገቢዎች ስለሚገኙበት ሁኔታ አጥንቶ ለወረዳው ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል።

በ. በወረዳው ምክር ቤት እና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በመንግስታዊ ስልጣናቸው ለሚፈጽሙት ተግባር እና ለሚያሳልፉት ውሳኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

አንቀፅ 84

ስለ ወረዳው አስተዳዳሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ከወረዳው ምክር ቤት አባላት መካከል አሸናፊ በሆነው ወይም አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት አቅራቢነት በወረዳው ምክር ቤት ይሠየማል።
2. በዚህ ሕገ መንግስት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የወረዳው አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

አንቀፅ 85

የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለወረዳው ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሆኖ የተሾመበት ወረዳ መስተዳድር ተጠሪና የአስተዳደሩ ሥራ መሪ ነው።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የሠፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው፡-

ሀ. የወረዳውን መስተዳድር ይወክላል።

ለ. የወረዳውን መስተዳድር ምክር ቤት ይሰበሰባል ይመራል።

ሐ. የፌዴራሉንና የክልሉን መንግስት ፖሊሲዎች ሕጐች፣ ደንቦች መመሪያዎችና፣ ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

መ. ምክትል አስተዳዳሪውን ጨምሮ የወረዳውን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለወረዳው ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል።

ሠ. የወረዳ መስተዳድሩን ልዩ ልዩ ተቋማትና በስሩ የሚገኙትን ቀበሌዎች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል ይቆጣጠራል።

ረ. የወረዳው ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና እቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል።

ሰ. የወረዳው ነዋሪ ሕዝብ ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ሕግና ስርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል።

ሸ. ለወረዳው ምክር ቤት፣ ለወረዳው መስተዳድር ም/ቤት እና ለበላይ የመስተዳድር አካላት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል።

ቀ. በወረዳው ምክር ቤት እና በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀፅ 86

የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ

1. የወረዳ አስተዳዳሪው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።
2. በወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

አንቀፅ 87

የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ጽሕፈት ቤት

1. የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።
2. የዋና አስተዳዳሪው ጽሕፈት ቤት የወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ቁምር ሊያገለግል ይችላል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሠናል።

ምዕራፍ ዘጠኝ

ስለ ቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን

አንቀፅ 88

አደረጃጀት እና ተጠሪነት

የቀበሌ አስተዳዳር የክልሉ የመጨረሻው መንግስታዊ አስተዳዳር እርከን ሲሆን በዚህ ሕገ መንግስት መሠረት ተጠሪነቱ እንደሁኔታው ለታቀፈበት የወረዳ ወይም የከተማ መስተዳደር ይሆናል።

የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉትን አበይት አካላት ይኖሩታል።

ሀ. የቀበሌ ምክር ቤት

ለ. የመስተዳድር ምክር ቤት

ሐ. የማህበራዊ ፍርድ ቤት

አንቀፅ 89

ስለ ቀበሌ ምክር ቤት

1. የቀበሌ ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግስት መሠረት የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ ተቋቁሟል።
2. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ።
3. የምክር ቤቱ አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ነው።
4. የቀበሌው ምክር ቤት ተጠሪነቱ እንደ ሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት የከተማ ምክር ቤት ወይም ወረዳ ምክር ቤት ይሆናል።

አንቀፅ 90

የቀበሌ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የወረዳው ምክር ቤት እና የወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት በየጊዜው የሚያወጧቸውን መመሪያዎች እና እቅዶች በቀበሌው ውስጥ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።
2. የበላዩ የሆኑት የአስተዳደር አካላት ከሚያወጧቸው ፖሊሲዎች ሕጎች ደንቦች እና መመሪያዎች ጋር በማይቃረን መንገድ የአካባቢ ማህበራዊ ጉዳይ መመሪያዎችን አውጥቶ በቀበሌው ውስጥ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።
3. ከቀበሌው ምክር ቤት አባላት መካከል አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤና የቀበሌውን አስተዳዳሪ ይመርጣል የቀበሌውን መስተዳድር ምክር ቤትም ያደራጃል።
4. በቀበሌው አስተዳዳሪ የሚቀርቡለትን የቀበሌውን ምክትል አስተዳዳሪና የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ያፀድቃል።

5. የበላዩ በሆኑ የአስተዳደር አካላት የሚሰጡትን የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ልማት እና አስተዳደራዊ እቅዶችንና ኘሮግራሞችን መሠረት በማድረግ የስራ አፈፃፀም መርሀ ግብር ያወጣል አፈፃፀሙንም ይከታተላል።
6. የቀበሌውን የመስተዳድር ምክር ቤትና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን የስራ ክፍፍልና ምደባ ይወስናል።
7. ለቀበሌው ሕዝብ የሚጠቅሙ ሌሎች ተጨማሪ እቅዶችን ያወጣል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል።
8. የቀበሌውን ሕዝብ ለልማት ስራ ያነሳሳል፣ የተፈጥሮ ሀብትን ልማት እና እንክብካቤ ሥራ ይከታተላል።
9. በቀበሌው ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል።

አንቀፅ 91

ስለ ቀበሌ ምክር ቤት አመራር

1. የቀበሌ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል በሚመረጡ አንድ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ ይመራል።
2. አፈ-ጉባኤው ምክር ቤቱን ይሰበሰባል፣ ይመራል አጀንዳዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ቃለ ጉባኤ መያዛቸውንና ሰነዶች መጠበቃቸውን ይቆጣጠራል።
3. ምክትል አፈ-ጉባኤው በአፈ-ጉባኤው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል አፈ-ጉባኤው በማይገኝበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሠራል።

አንቀፅ 92

የቀበሌ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜና የስራ ዘመን

1. የቀበሌ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያካሂዳል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከሁለት ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤት አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።
3. የቀበሌው ምክር ቤት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የስራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የስራ ዘመን በተጠናቀቀ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።
4. የቀበሌው ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል። ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆነው አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ-ጉባኤው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

አንቀፅ 93

የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት አወቃቀር

1. የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት የቀበሌው አስተዳዳሪ ምክትል አስተዳዳሪና በቀበሌው ውስጥ ከሚገኙ የማህበራዊ አገልግሎት ሠጭ የመንግስት ተቋማት ሠራተኞች በአባልነት የሚገኙበት የበታች አስፈፃሚ አካል ነው።
2. የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌው አስተዳዳሪና ለቀበሌው ምክር ቤት።
3. የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት አባላትና በግልና በወል የቀበሌውን አስተዳደር ሥራ ይመራሉ፣ ያስተባብራሉ።
4. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በጋራ ስልጣናቸው ለሚያሳልፉት ውሳኔና ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

አንቀፅ 94

የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ. የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት የልማት እቅዶችንና ኘሮግራሞችን ያወጣል፣ ለቀበሌው ምክር ቤት እያቀረበ ያፀድቃል፣ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።

ለ. የገጠር ልማትን ያፋጥናል፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንክብካቤና ልማት ስራ እንዲካሄድ ያደርጋል ሕዝቡንም ለልማት ስራ ያነሳሳል፣ ያስተባብራል።

ሐ. የቀበሌው ሰላምና ፀጥታ እንዲጠበቅ ያደርጋል። የስራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል።

መ. በቀበሌው ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ዝርዝር የሥራ እቅዶችን የሚነድፈውና አፈፃፀማቸውን የሚከታተለውም ሆነ የሚገመግመው እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው እየተገናኘ ይሆናል።

አንቀፅ 95

ስለቀበሌው አስተዳዳሪ አሰያየምና የስራ ዘመን

1. የቀበሌው አስተዳዳሪ ከቀበሌው ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል።
2. በዚህ ሕገ መንግስት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌ አስተዳዳሪው የስራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የስራ ዘመን ነው።

አንቀፅ 96

የቀበሌ አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

1. የቀበሌው አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤትና እንደ ሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት የወረዳ ወይም ከተማ መስተዳደር ሆኖ የቀበሌው ሊቀመንበር የመስተዳድሩ ስራ መሪ የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሠፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌው አስተዳዳሪ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ. የቀበሌውን የመስተዳድር ምክረ ቤት ይሠበሰባል ይመራል።

ለ. የበላይ በሆኑት የአስተዳደር አካላት የሚወጡትን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና እቅዶች ተቀብሎ በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።

ሐ. የቀበሌውን ምክትል አስተዳዳሪ እና የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ለቀበሌ ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል።

መ. በቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት በቀበሌው ምክር ቤት እና እንደሁኔታው በሚመለከተው ከተማ ወይም ወረዳ መስተዳድር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

አንቀፅ 97

የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ በቀበሌ አስተዳዳሪ ተመርጦ ሹመቱ በቀበሌው ምክር ቤት የሚፀድቅ ሆኖ

1. በቀበሌው አስተዳዳሪና በመስተዳድሩ ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
2. የቀበሌው አስተዳዳሪ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።
3. የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው አስተዳዳሪና ለመስተዳድሩ ምክር ቤት ነው።

አንቀፅ 98

ስለ ቀበሌ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት

1. የቀበሌ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት የመስተዳድር ምክር ቤትም ጭምር ሆኖ ያገለግላል።
2. የቀበሌ ምክረ ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት እስከሚኖረው የቀበሌ አስተዳደሩን ጽሕፈት ቤትና የቢሮ መገልገያዎች በመጋራት ይሠራል።

አንቀፅ 99

የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

1. የቀበሌው ማህበራዊ ፍርድ ቤት በዚህ ሕገ መንግስት የቀበሌው ማህበራዊ የዳኝነት አካል ሆኖ ተቋቁሟል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
2. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በዚህ ሕገ መንግስት አንቀፅ 90 ንዑስ አንቀፅ 4 ስር በተደነገገው መሠረት ተመርጠው የሚሾሙ ይሆናሉ።
3. የማህበራዊ ፍርድ ቤት የስራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የስራ ዘመን ነው።

ምዕራፍ አስር

የክልሉ ፖሊሲ አላማዎች

አንቀፅ 100

አላማዎች

1. ማንኛውም የመንግስት አካል የፌዴራሉንና የክለሉን ህገ መንግስት፣ ሌሎች ህጎችና ፖሊሲዎችን በስራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት አላማዎች እና መርሆዎች ላይ መመስረት አለበት።
2. በዚህ ምዕራፍ መንግስት ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ይሆናል።

አንቀፅ 101

ፖለቲካ ነክ አላማዎች

1. መንግስት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት የአፋር ክልል ህዝብ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።
2. መንግስት የብሔረሰቦችና የህዝቦች ማንነት የማክበር በዚህ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው አኩልነትን አንድነትን ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት።

አንቀፅ 102

ኢኮኖሚ ነክ አላማዎች

1. መንግስት ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ በተጠራቀመ እውቀትና ሀብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት።
2. የክልሉ ኢኮኖሚ በዋነኛነት የተመሠረተው በእንስሳት ሀብት በመሆኑ መንግስት ፖሊሲዎችንና ኘሮግራሞችን ሲቀርፅ የአርብቶ አደሩን የኑሮ መሠረት በማሻሻል ወደ ተረጋጋ ኑሮ የሚመጣበትንና የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።
3. መንግስት የክልሉን ነዋሪዎች የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል እድገት እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት
4. መንግስት የተፈጥሮና የሠው ሠራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጎጂው እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ አለበት።
5. መንግስት የክልሉን ኢኮኖሚ ከሀገር አቀፍ ኢኮኖሚ ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ከፌዴራል መንግስት አካላት ጋር ጥረት ያደርጋል።
6. መንግስት የግል ባለሀብቶችን በክልሉ ልማት እንዲሳተፉ ያበረታታል፣አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል።
7. መንግስት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በህዝብ ስም በፀዙታው ስር በማድረግ ለህዝቡ የጋራ ጥቅምና እድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።
8. መንግስት የክልሉ የልማት ፖሊሲዎችና ኘሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት ህዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት። የህዝቡንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት።
9. መንግስት የህዝቡን እውቀት ጉልበትና ገንዘብ በማቀናጀት ፈጣን ልማት የሚረጋገጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት። ህዝቡ በክልሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረው ማድረግ አለበት። ስለሆነም ህዝቡ እቅዶችና ፖሊሲዎችን ለመደገፍ ብቻ ሳይሆን በማስፈፀምና በመገምገም መሳተፍ አለበት።
10. መንግስት በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የሚሳተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።
11. መንግስት የሠራተኛውን ሕዝብ ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት።

አንቀፅ 103

ማህበራዊ አላማዎች

1. የአገሪቱና የክልሉ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የትምህርት የጤና አገልግሎት የንፁህ ውኃ የመኖሪያ የምግብና የማህበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው ያደርጋል።
2. ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከሀይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶች፣ ከባህላዊ ተጽዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ ይካሄዳል።

አንቀፅ 104

ባህል ነክ አላማዎች

1. የክልሉ መንግስት መሠረታዊ መብቶችንና ሰብአዊ ክብርን ዲሞክራሲንና ህገ መንግስቱን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲንሰብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።
2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የያንጉዲራሳና የአዋሽ ፖርኮችን የፌዴራሉ መንግስት ከሚያደርገው ጥበቃ በተጨማሪ የክልሉ መንግስት ህዝብ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው።
3. የክልሉ መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን ሳይንስና ቴክኖሎጂን ማስፋፋት ግዴታ አለበት።
4. መንግስት ወጣቱን ትውልድ የመንከባከብ በተሟላ ሥነ ምግባር የማነፅ፣ ከሱስ ነፃ የሆነና፣ በአካልም ሆነ በአእምሮ ጠንክሮ ኃላፊነትን የሚሸከም፣ አገሩን የሚወድ እና ለወገኑ የሚቆረቆር ብቁና በራሱ የሚተማመን ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት አለበት።
5. የክልሉ የሥራ ቋንቋ ለሆነው የአፋር ቋንቋ እድገት መንግስት ልዩ ትኩረት በመስጠት ይንቀሳቀሳል።
6. የክልሉ መንግስትና ህዝብ በክልሉ ውስጥ ያገኙትን የአርኪኦሎጂ ግኝቶችና የታሪክ ቅርሶችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።

አንቀፅ 105

የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ አላማዎች

1. መንግስት ሁሉም የክልሉ ነዋሪ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት።
2. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት።
3. የህዝብን የአካባቢ ደህንነት በሚመለከት ፖሊሲና ኘሮግራም በሚነደፍበትና ስራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ህዝብ ሁሉ ሃሳቡን እንዲገልፅ ማድረግ አለበት።
4. መንግስት የክልሉ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው። በተለይ በረሃማነትን ለመከላከልና ለመግታት መንግስትና ህዝብ አስፈላጊውን ሁሉ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

ምዕራፍ አስራ አንድ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀፅ 106

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

1. በፌዴራሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 93 ንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ) እና (ለ) እና በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ 45 ንዑስ አንቀፅ 2 (ወ) በተደነገገው መሠረት ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ባልሆነበት ጊዜ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ህገ መንግስት አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀፅ (7) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል።
2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌውን አውጥቶ በስራ ላይ ባዋለ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ አፈ-ጉባኤው የክልሉን ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ማሳወቅና የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን ለምክር ቤቱ በማቅረብ ማፅደቅ አለበት።
3. የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ያወጣው የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በክልሉ ምክር ቤት ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለው ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ሲወስን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን በየአራት ወሩ እንዲታደስ ለማድረግ ይችላል። ይህን በስራ ላይ ማዋል የሚችለው ግን ለሶስት ጊዜ ብቻ ነው።
4. የክልል መስተዳድር ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ የሚያወጣቸው ደንቦችና የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 16 አንቀፅ 18 (1) እና (2)፣ 21(1)፣ 24(1)፣ 27(1) እና 39 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም።

አንቀፅ 107

የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ

1. የክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና ከህግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሶስት የቦርዱ አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ መርማሪ ቦርድ መቋቋም ይችላል። ቦርዱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በክልል ምክር ቤት በሚፀድቅበት ጊዜ ይቋቋማል።
2. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

ሀ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ምክንያት የታሠሩትን ግለሰቦች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ማድረግና የታሠሩበትን ምክንያት መግለፅ።

ለ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ወቅት የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ ኢሰብአዊ አለመሆናቸውን መቆጣጠርና መከታተል፣

ሐ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እርምጃዎች ኢሠብአዊ ድርጊት የፈፀሙት ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ፣

መ. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እንዲቀጥል ለክልሉ ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለውን አስተያየት ለምክር ቤቱ ማቅረብ።

አንቀፅ 108

የክልሉ ዋና ኦዲተር

1. የክልሉ ዋና ኦዲተር በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማል።
2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉ መንግስት ተቋማትና ሌሎች መስራያ ቤቶችን ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልል ምክር ቤት የተመደበው አመታዊ በጀት በበጀት አመቱ ውስጥ እንዲሠሩ ለተወሰኑት ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።
3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመስሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል።
4. የዋና ኦዲተር ተጠሪነት ለክልል ምክር ቤት ይሆናል።
5. የዋና ኦዲተር ዝርዝር ስልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል።

አንቀፅ 109

የህገ መንግስት ማሻሻያ ሀሳብ ስለማመንጨት

የዚህ ህገ መንግስት ማሻሻያ ሃሳብ አጀንዳ ሆኖ ለውይይት የሚቀርበው፦

ሀ. በክልሉ ምክር ቤት አባላት አንድ ሶስተኛ ጥያቄ ወይም

ለ. በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአብላጫ ድምፅ ውሳኔ ወይም

ሐ. በክልሉ ውስጥ ካሉ የወረዳ ምክር ቤቶች በአንድ ሶስተኛው ጥያቄ ወይም

መ. በክልሉ ውስጥ ካሉ የቀበሌ ምክር ቤቶች በአንድ ሶስተኛው የተጠየቀ ከሆነ ለውይይትና ለውሳኔ የህገ መንግስቱ መሻሻል ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይቀርባል።

አንቀፅ 110

የህገ መንግስት ማሻሻል

1. የዚህ ህገ መንግስት ምዕራፍ ሁለትና ሶስት የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚሻሻሉት በፌዴራል ህገ መንግስት አንቀፅ 105 መሠረት በማድረግ የሆናል።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት የህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል።

ሀ. በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት የወረዳ ምክር ቤቶች ከግማሽ በላይ የማሆኑት በአብላጫ ድምፅ ሲያፀድቁት።

ለ. በክልሉ ምክር ቤት አባላት በሶስት አራተኛ ድምፅ ሲያፀድቁት ነው።

3. የዚህ ንዑስ አንቀፅና የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ሁለት ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት የቀረበውን ማሻሻያ

ሀ. በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳ ምክር ቤቶች ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ብልጫ ሲያፀድቁት ነው።

ለ. የክልሉ ምክር ቤት በሶስት አራተኛ ድምፅ ሲያፀድቁት ነው።

አንቀፅ 111

የመጨረሻ ህጋዊ ኮፒ

የዚህ ህገ መንግስት የአፋርኛ ቅጅ የመጨረሻው ህጋዊ እውቅና ያለው ሠነድ ነው።